# ለመክሰስ ፡ መብተኛ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብ ፡ ብቻ ፡ የክሱን ፡ ጕዳይ ፡ ለመከታተል ፡ የሚቻልባቸው ፡ ወንጀሎች ።

ክፊሊፕ ፡ ግራቨን ፡
ፍርድ ፡ ሚኒስቴር ።

የ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። "የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ግብ ፡ ስለ ፡ ጠቅላላው ፡ ጥቅም ፡ ሥርዐትን ፡ ሰላምን ፡ የመንግሥትንና ፡ የዜጎችን ፡ ጸጥታ ፡ መጠበቅና ፡ ማረጋገጥ ፡ ነው ።" የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ይህንን ፡ ግብ ፡ የሚፈጽመው ፡ ስለ ፡ ጠቅላላው ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ ሊደረጉ ፡ የማይገባቸውን ፡ እንዳይደረጉ ፡ ሊደረጉ ፡ የሚገባቸውን ፡ እንዲደረጉ ፡ ያለማድረግ ፡ ክልከላዎችን ፡ ወይም ፡ የማድረግ ፡ ግዴታዎችን ፡ በመመደብ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እነዚህን ፡ ክልከላዎች ፡ ወይም ፡ ግዴታዎች ፡ አፍርሶ ፡ የሚገኝ ፡ ሁሉ ፡ ለጠቅላላው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በኀላፊነት ፡ ያስጠይቀዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። መንግሥት ፡ በሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ለዜጎች ፡ ተወክሎ ፡ የወንጀልን ፡ ጕዳይ ፡ እንዲከታተልና ፡ ክሶ ፡ እንዲያስቀጣ ፡ ኀላፊነቱ ፡ ሊወድቅበት ፡ የቻለውም ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የጠቅላላውን ፡ ሕዝብ ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታ ፡ የማያደፈርሱ ፡ ወንጀሎች ፡ አሉ ። እነሱም ፡ በተለይ ፡ ጥቅማቸው ፡ የተነካባቸውን ፡ ወይም ፡ የተበደሉትን ፡ ሰዎች ፡ መብት ፡ ብቻ ፡ የሚመለከቱ ፡ ወንጀሎች ፡ ናቸው ። የእነዚህ ፡ ወንጀሎች ፡ አፈጻጸም ፡ ውጤት ፡ ከተጐዳው ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ በላይ ፡ አልፎ ፡ የሌሎችን ፡ ጥቅምና ፡ ጕዳት ፡ የማይመለከት ፡ ወይም ፡ የማይነካ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በጠቅላላው ፡ ተበዳዩ ፡ ቢስማማ ፡ ባይስማማም ፡ የወንጀል ፡ ክስን ፡ መከታተል ፡ የመንግሥት ፡ ኀላፊነት ፡ ቢኾንም ፡ ቅሉ ፡ በንደዚህ ፡ ባሉት ፡ ነገሮች ፡ የተጐዳው ፡ ሰው ፡ በዳዩ ፡ ተከሶ ፡ በፍርድ ፡ እንዲታይለት ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኑን ፡ በእርግጥ ፡ ካላሳየ ፡ በስተቀር ፡ መንግሥት ፡ ይህንን ፡ ግዳጁን ፡ አያከናውንም ።

የተበደለው ፡ ሰው ፡ ስምምነት ፡ በቅድሚያ ፡ የሚያስፈልግበትም ፡ ምክንያት ፡ አንደኛ ፡ ወንጀሉ ፡ ጠቅላላውን ፡ የሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ስለማይመለከት ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ባለመንካቱ ፡ ኹለተኛ ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ ሳይስማማበት ፡ ክስ ፡ ቢቀርብ ፡ ስራሱ ፡ ለተበደለው ፡ ሰው ፡ ጕዳትን ፡ ስለሚያመጣበት ፡ ነው ። ጕዳትም ፡ የሚያመጣው ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ በክሱ ፡ ምክንያት ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ በይፋ ፡ ሊታወቅበት ፡ የማይፈልገው ፡ ጕዳይ ፡ ሊኖር ፡ በመቻሉ ፤ ወንጀሉ ፡ በአደባባይ ፡ ቢታይ ፡ የወንጀሉ ፡ ተግባር ፡ ካደረሰበት ፡ በደል ፡ የበለጠ ፡ ጕዳት ፡ ክሱን ፡ በማንቀሳቀስ ፡ ሊደርስበት ፡ ስለሚችል ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የክሱ ፡ ጕዳይ ፡ የሚስቱን ፡ አለመታመን ፡ የልጁን ፡ ወስላታነት ፡ በአደባባይ ፡ ሸንጎ ፡ ያወጣበት ፡ ይሆናል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ሊንቀሳቀስ ፡ የሚችለው ፡

